# <u>የፖለቲካ ሽሙጥ</u>

*ከአስተዋይ በቀለ*

*እንዲያው የጉድ እኮ ነው ! ስንቱ ይሰማል !*

*እነ አቶ ደነቀው አዲስ አበባ ላይ የጥቂት መሳፍንቶችን የዝርፊያ ከተማ አይተው ኢትዮጵያ ደርሰን መጣን ይላሉ። ይህ አልበቃቸው ብሎ እንደ አድር ባይ ወዶ - ገባ ጭራቸውን እየቆሉ ፎቁ፣ ቀለበት መንገዱ፣ ድልድዩ እረ ስንቱ ! ልማት የጉድ ነው እያሉ ይቀደዳሉ።*

*እነዚህ አሞካሾች አንጎላቸው ወጥቶ በምትኩ ጋራጋንቲ ተሞልቶ ልሾ የተደረገ ጭንቅላት ያላቸው ገልቱዎች ሆነው ነው እንጂ፤ ፋሽስት ጣሊያንም እኮ እንደ ወያኔ በጠመንጃ ኢትዮጵያን ወርሮ ሕዝቦቿን በቦምብ እየገደለና በመርዝ ጭስ እያቃጠለ መንገድም፣ ድልድይም፣ ግድብም፣ ፎቆም ሰርቷል።*

*አገር ወዳድ ልብ በል !*

*በጠበንጃ በጉልበት ይዘው እየገደሉና እየዘረፉ መገንባት የፋሽስቶች ባሕሪ ነው። ግንባታው ለጥቂቶቹ ጥቅምና ሞኖፖል ሲሆን፤ አብዛኛው ሰፊ ሕዝብ ግን በረጂም ዘመን ታሪኩ አይቶት በማያውቀው ባርነት ተረግጦ በደዌ፣ በረሃብና በስደት እየተሰቃየ ነው።*

*ፍሽስት ጣሊያን አበሻ አገር ዳግመኛ እንዳይደርስ እንደተፈጸመ ሁሉ ሌላውም የአገር ውስጥ ፋሽስት ይፈጸማል።*

*ያኔ የተገነባውና የተዘረፈው ሁሉ ያገር ጥቅምና ንብረት ይሆናል።*

*በየትኛውም የዓለም ክፍልና አገር በተለያዩ መንገዶችንና ስልቶች የተሰወረው ገንዘብ፣ ንብረትና ወንጀለኛ ሁሉ በኢትዮጵያ ረጅም ክንድ እየተለቀመ ወደ እናት አገር ይመለሳል።*

*የጊዜ ጉዳይ ነው ! ሕዝብ ያሸንፋል አገር ይረጋገጣል።*